## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

## የ6ኛ ክፍል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ሰርተፊኬት ፈተና

## አማርኛ, ሰኔ 2017ዓ.ም/ *JUNE* 2025G.C

የጥያቄ ብዛት: 40 የተፈቀደው ሰዓት: - 1 ሰዓት

አጠቃላይ ትዕዛዝ

ይህ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል። በፈተና ላይ የተሰጡትን ትእዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል። መልስ የሚሰጠው ለብቻ በተዘጋጀው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው ። በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ በማጠጥቆር የሚመለስ ሲሆን የሚሰራው በእርሳስ ብቻ ነው። ትክክለኛውን መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት። የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት።

መልስ የሚሰጠው በመልስ መስጫው ላይ ብቻ ነው ። ለምሳሌ መልሳችሁ "መ" ከሆነ ከታች በሚታየው መልክ ማጥቆር አለባችሁ

| ሀ | ለ | ሐ | መ |
|---|---|---|---|
| ○ | ○ | ○ | ● |

ፈተናውን ሰርቶ ለመጨርስ የተፈቀደው 1 ሰአት ነው። ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናው መስራት ማቆም አለብን። ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን።

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰአት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል።

ፈተናውን መስራት ከመጀመራቹሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባቸውን መረጃዎች ሁሉ በጥንቃቄ መሙላት አለባችሁ።

**ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም**

LIVEWORKSHEETS

## ምንባብ

ባህል ለሚለው ቃል ውስን ያለ ብያኔ ሲሰጠው አይታይም፡፡ ብዙዎቹ በተለያየ መንገድ ለመበየን ሞክረዋል፤ ነገር ግን ሁሉንም ሊያስማማ የሚችል ወጥ የሆነ ግንዛቤ ላይ አልተደረሰም፡፡ የተወሰኑትን ለማየት ብንሞክር፡- ባህል የህብረተሰብ የአኗኗር፣ ዘይ፣ ወግ፣ልማድ፣ እምነት ነው፡፡ ሌላው ብያኔ ውስብስብና ሁሉንም መንፈሳዊ፣ ቁሳዊ፣ አእምሯዊ እና ስሜታዊ ባህሪያትን የያዘ የአንድ ህብረተሰብ መገለጫ ነው፡፡ በየቀኑ የምንሰራው ስራም ባህል ነው፤ ነገር ግን ባህል ጥበባዊ ነገሮችን ብቻ አይዳስስም ይልቁንም የሰውን ልጅ መሰረታዊ መብቶችን፣የአኗኗር ሁኔታዎችን፣ እሴቶችን፣ ልማዶችንና እምነቶችን አቅፎ ይይዛል፡፡

ዘረፈ ብዙ ብያኔ የተሰጠው ባህል የተለያዩ መገለጫዎች ወይም ባህሪያት አሉት፡፡ ከባህሪያቱ መካከል፡- ባህል ይለወጣል፣ ባህል መልከ ብዙ ነው፣ ባህል በአውድ የተከበበ ነው፣ባህል በማህበራዊ ሁኔታዎች የሚፈጠር እና የሚመሰረት ነው፣ ባህል የምንማረው ነው፣ባህል በሥነ ህይወት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፣ ባህል ተገላጭ ነው እንጂ ተገምጋሚ ጽንሰ ሐሳብ አይደለም፣ ወዘተ ናቸው፡፡

ባህል ይለወጣል ሲባል ሰዎች ለመኖር ሲሉ የተለያዩ ተለዋዋጮችን በአንድነት በሚጠቀሙበት፣ በተሳታፊዎች ተራክቦ ቀጣይነት ባለው መንገድ እየተለዋወጠ እንደገና ይፈጠራል፡፡ በአካባቢው በሚደርሰው ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ለውጥ የተነሳ ሁልጊዜ፣ ይቀየራል፡፡ እንደአብነት ቀደም ሲል እንጀራ ሳይቆረስ ለማዕድ ይቀርባል፤ ከዚያም የሐይማኖት አባቶች ካሉ እነሱ ከሌሉ ደግሞ አባወራ ወይም ወንዶች መጀመሪያ ከባረኩት በኋላ ማዕዱ ይጀመራል፡፡ ይህን በተመለከተ ሽግግሩ ማለትም ካለመቆረስ ወደ መቆረስ በተካሔደበት ጊዜ ክርክሮች እንደነበሩ የሚታወስ ነው፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን መቆረሱ ከኢኮኖሚ፣ ከጤና፣ ከጉልበት፣ ከማህበራዊ ፍላጎት አንጻር ጠቃሚነቱ እየታወቀ በመሔዱ የተነሳ በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል እየተለመደ መጥቷል፡፡

ባህል መልከ ብዙ ነው ሲባል አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ካንድ በላይ ለሆኑ ባህሎች መጋለጥ መቻሉን ያሳያል፡፡ ባህል የቡድኖች ስለሆነ ባንድ ቡድን ውስጥ ደግሞ የተለያዩ ባህሎች አሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ ቡድኖች ደግሞ ተፈጥሮን ለመጋፈጥና ለመኖር ሲሉ የፈጠሯቸው(የስራ፣ የአኗኗር፣ የአመጋገብ፣ የአለባበስ፣..) ማንነቶች አሉ፡፡ ግለሰቡም በአካባቢው ለሚገኙ የቡድን ማንነቶች ተጋላጭ ነው፡፡ ስለዚህ በኩል ደረጃ እንኳ ባይጠቀምባቸውም በማህበረሰቡ ውስጥ እስካለ ድረስ ከሁሉም ዓይነት ባህሎች ጋር መነካካቱ አይቀሬ ነው፡፡ ይህም የባህልን መልከ ብዙነትን ያሳያል፡፡

ባህል በአውድ የተከበበ ነው ሲል አንድ ባህል በውስጣዊም ሆነ በውጫዊ ተለዋዋጭ ቁጥጥር ውስጥ ነው፡፡ ማለትም በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ ተላውጦዎች የተነሳ ተፅዕኖ ይደርስበታ፡፡ ለምሳሌ የተከበሩ



LIVEWORKSHEETS

እሴቶች፣ ቋንቋዎች፣ ቀበሌኛዎች ክብርን ያገኙት ያበጁዋቸው ማህበረሰቦች የበላይ በመሆናቸው እንጂ እነዚህ እሴቶች ቋንቋዎች በራሳቸው ከሌሎች የተሻሉ ወይም ያነሱ ሆነው አይደለም።

ምንጭ፡- አለማየሁ ተመስገን ዶ/ር (2015፣ ባህልና አፈንጋጭነት፣

ከገጽ1/28 ለክፍል ደረጃው እንዲመጥን ተደርጎ የተወሰደ)

**መመሪያ አንድ፡-** ከጥያቄ 1 እስከ 13 ያሉ ጥያቄዎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው፤

እንደአጠያየቃቸው መልስ ስጡ።

1. ስለባህል ትክክል የሆነው አገላለጽ የቱ ነው?
   ሀ. ከህብረተሰቡ ተነጥሎ የሚታይ ነው።
   ለ. የማህበረሰብ የህይወት ስርዓት ማሳያ ነው።
   ሐ. ቋሚና የማይለወጥ ነው።
   መ. ዋና ትኩረቱ ጥበባዊ ጉዳዮች ላይ ነው።

2. "ባህል ተገላጭ እንጂ ተገምጋሚ ጽንሰ ሐሳብ አይደለም።" ማለት
   ሀ. ትክክል ወይም ስህተት ብሎ መፈረጅ እንደማይቻል ያሳያል።
   ለ. ጎጂ ባህል እንዳለ ሁሉ ጠቃሚ ባህል መኖሩን ያሳያል።
   ሐ. ጎጂ ባህሎች ተወግደው ጠቃሚዎቹን ማስቀጠል እንዳለብን ያስገነዝባል።
   መ. እንቅስቃሴዎች ሁሉ ባህል መሆናቸውን ይጠቁማል።

3. የአንቀጽ ሁለት መሰረታዊ ተግባር ምንድን ነው?
   ሀ. ስለባህል የተሰጡ ብያኔዎችን ማብራራት
   ለ. ባህል ሊባሉ የሚችሉ ነገሮችን መዘርዘር
   ሐ. የባህል መገለጫዎችን መዘርዘር
   መ. ባህል እንዳይበረዝ ግንዛቤ መፍጠር።



LIVEWORKSHEETS

4. ከሚከተሉት አንዱ በአንቀጽ ሶስት ውስጥ የተገለጸን ሐሳብ አልያዘም፡፡
   ሀ. ባህል በተለያዩ ተለዋዋጮች አማካይነት እንደገና ይፈጠራል፡፡
   ለ. ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጦች ባህልን ይቀያይሩታል፡፡
   ሐ. የተሳታፊዎች ተራክቦ ባህልን እንዲለወጥ ያደርጋል፡፡
   መ. ስለሰው ልጅ መሰረታዊ መብት ያስረዳል፡፡
5. ከላይ የቀረበው ምንባብ መሰረታዊ ትኩረቱ ምንድን ነው?
   ሀ. ባህል መለወጥ እንደሌለበት ያሳያል፡፡
   ለ. የባህል መገለጫዎችን ማስገንዘብ፡፡
   ሐ. ባህል ለለውጥ ዝግጁ መሆኑን ማስረዳት
   መ. ልክና ስህተት የሚባል ባህል አለመኖሩን መንገር
6. የአንቀጽ አራት ዋና ሐሳብ ምንድን ነው?
   ሀ. በአንድ ቦታ ብዙ አይነት ባህሎች መኖራቸውን
   ለ. ግለሰቦች ከአንድ በላይ ለሆኑ ባህሎች መጋለጣቸውን
   ሐ. የባህል ባህሪያትን ማሳየት
   መ. የባህልን ምንነት ማስረዳት
7. በአንቀጽ ሶስትና አራት መካከል መሸጋገሪያ ሆኖ ያገለገለው የቱ ነው?
   ሀ. የባህል መገለጫዎች
   ለ. የሰው ልጅ የሰራው ሁሉ ባህል መሆኑ
   ሐ. በአውድ መከበቡ
   መ. የባህል ለውጥ ማስረጃ መሆኑ
8. ከላይ የቀረበው ምንባብ ምን ዓይነት ድርሰት ነው?

   ሀ. ተራኪ  ለ. ገላጭ  ሐ. አስረጂ  መ. አመዛዛኝ

9. ከላይ ለቀረበው ምንባብ ርዕስ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?
   ሀ. ባህልና ዓይነቶቹ
   ለ. ባህልና ትርጓሜዎቹ
   ሐ. ባህልና መገለጫው
   መ. ባህልና ጥቅሞቹ



LIVEWORKSHEETS

10. መጋፈጥ ለሚለው ቃል አውዳዊ ፍቺ

ሀ. መሸሽ ለ. መፋለም ሐ. መስማማት መ. መተው

11. አብነት ለሚለው ቃል አውዳዊ ፍቺ

ሀ. ትልቅ ለ. ምሳሌ ሐ. የሰፈር ስም መ. ዋና

12. ማዕድ ለሚለው አውዳዊ ፍቺ

ሀ. ልማድ ለ. የተፈጥሮ ሐብት ሐ. እሴት መ. ምግብ

13. መገለጫዎች በምዕላድ ተነጣጥሎ ሲጻፍ

ሀ. መግለጫ-ኣ- ዎች

ለ. መግለጫ-ዎች

ሐ. መግለ-ጭዎች

መ. መግለጭ-ዎች

***መመሪያ ሁለት፡-*** ከጥያቄ 14 እስከ 21 ያሉትን ጥያቄዎች በአጠያየቃቸው መሰረት መልሱ።

14. ስለአንቀጽ አካላት ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. በመግቢያው ውስጥ ዋና ዋና ሐሳቦች ይብራራሉ።

ለ. በማጠቃለያ ክፍሉ የተዘነጉ ነጥቦች ይነሳሉ።

ሐ. በመግቢያው ላይ ስለሚነሱ ነጥቦች ጥቆማ ይሰጣል።

መ. በሐተታው ክፍል ዋና ዋና ነጥቦች ተጨምቀው ይገባሉ።

15. የሚከተለውን ቅንጭብ በማንበብ የድርሰት ዓይነቱን ለዩ።

የተወለደችው የዛሬ 13 ዓመት ገደማ ሲሆን እናትና አባትዋን በመኪና አደጋ አጣቻቸው። ከዚያም በጉዲፈቻ ወደ ጣሊያን ሀገር ተሰደደች።

ሀ. ተራኪ ለ. ገላጭ ሐ. አመዛዛኝ መ. አስረጂ

16. ትክክለኛውን የግል ደብዳቤ የአጻጻፍ ቅርጽ **ያልያዘው** የቱ ነው?

ሀ. በደብዳቤው መጨረሻ ቁጥር ይጻፋል

ለ. በመግቢያው ሰላምታ ይገለጻል

ሐ. በግራ ራስጌ በመጀመሪያ የተቀባይ ስም ይጻፋል

መ. በቀኝ ራስጌ ቀን ይጻፋል



LIVEWORKSHEETS

17. በትክክለኛው የምዕላድ አተናተን የተጻፈው የቱ ነው?

ሀ. ከምፒተር-ኦች-ኦች-ን

ለ. ቤተመኩራ-ዎች

ሐ. ልብስ-ኦች-ኦችሁ

መ. አባል-ኦች

18. ትክክለኛው የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም የቱ ነው?

ሀ. ሚኒስትሩ፣" የተማሪዎችን የመማር አቅም ለማሳደግ ዘመናዊ ግብዓቶችን (ቴክኖሎጂዎችን) በ2018 ዓ.ም እንጠቀማለን፡፡" አለ፡፡

ለ. ሚኒስትሩ፣" የተማሪዎችን የመማር አቅም ለማሳደግ ዘመናዊ ግብዓቶችን (ቴክኖሎጂዎችን) በ2018 ዓም እንጠቀማለን፡፡" አለ፡፡

ሐ. ሚኒስትሩ፣" የተማሪዎችን የመማር አቅም ለማሳደግ ዘመናዊ ግብዓቶችን ቴክኖሎጂዎችን በ2018 ዓ.ም እንጠቀማለን፡፡" አለ፡፡

መ. ሚኒስትሩ፣" የተማሪዎችን የመማር አቅም ለማሳደግ ዘመናዊ ግብዓቶችን (ቴክኖሎጂዎችን) በ2018 ዓ.ም እንጠቀማለን"፡፡ አለ፡፡

19. ሁለት ሐሳቦችን በመውሰድ ተራ በተራ የሚገልጽ የድርሰት ዓይነት

ሀ. ገላጭ ለ. አመዛዛኝ ሐ. ተራኪ መ. አስረጂ

20. የሚከተለውን ቅንጭብ አገልግሎቱ ምንድን ነው?

የሰው ልጅ ብዙ ምኞቶች አሉት፡፡ ከምኞቶቹ መካከል፡- አውሮፕላን አብራሪ መሆን፣የመድኃኒት ባለሙያ መሆን፣ አስተማሪ መሆን፣ ወታደር መሆን፣ወዘተ ናቸው፡፡ እነዚህን ምኞቶች ለማሳካት የሚሰራቸውን ተግባራት ቀጥሎ እናያለን፡፡

ሀ. መግቢያ ለ. መሸጋገሪያ ሐ. ሐተታ መ. መደምደሚያ

21. በግለሰብ ደብዳቤ ውስጥ **የማይካተተው** የቱ ነው?

ሀ. ቁጥር ለ. ቀን ሐ. ተቀባይ መ. ጉዳይ

**መመሪያ ሶስት፡-** ከጥያቄ 22 እስከ 29 ለቀረቡ የቃላት ጥያቄዎች ተገቢ የሆነ መልስ ስጡ፡፡

22. የእንከን ተመሳሳይ

ሀ. ነገር ለ. ችግር ሐ. ጥፋት መ. ኃጢአት

23. የራደ ተመሳሳይ

ሀ. ተቆጣ ለ. ተቀየመ ሐ. ፈራ መ. ተበሳጨ



LIVEWORKSHEETS

24. ስመለመ ለሚለው ተቃራኒ

ሀ. ጠወለገ   ለ. አፈራ   ሐ. ቅጠል አወጣ   መ. ተቀጠፈ

25. ልዩ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. አሽከር   ለ. ሎሌ   ሐ. አለቃ   መ. ጭፍራ

26. የጅብ ፍካሬያዊ ፍች

ሀ. የዱር እንስሳ   ለ. ሆዳም   ሐ. አስፈሪ   መ. ለፍላፊ

27. አባብ ለሚለው እማሬያዊ ፍች

ሀ. ተንኮለኛ የሆነ   ለ. ተሳቢ እንስሳ   ሐ. ብልጥ   መ. ተራማጅ እንስሳ

28. ጥምር ቃል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. አምባሳደር   ለ. መዝገበ ቃላት   ሐ ፍኖተ ካርታ   መ. አድሎኣዊ

29. እብድ ለሚለው ተቃራኒ

ሀ. የተረጋጋ   ለ. ወፈፌ   ሐ. የተቀወሰ   መ.ንክ

**መመሪያ አራት፡-** ከጥያቄ 30 እስከ 40 ሰዋስው ነክ የሆኑ ጥያቄዎችን በአጠያየቃቸው መሰረት መልሱ።

30. የወል ስም የሆነው

ሀ. የአባይ ግድብ   ለ. ህዝቅኤል   ሐ. መምህር   መ. አዲስ አበባ

31. መንገዶቻችን በሚለው ቃል ውስጥ ብዙ ቁጥር አመልካች ምዕላዱ የቱ ነው?

ሀ. መንገድ   ለ. -ኦች   ሐ. -ኣችን   መ. -ኦች-ኣችን

32. ሙሉጌታ በፍጥነት ወደትምህርት ቤት ሄደ። በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ተውሳከ ግስ የቱ ነው?

ሀ. ወደ   ለ. ትምህርት ቤት   ሐ. ተማሪ   መ. በፍጥነት

33. ትክክለኛው የአበዛዝ ሥርዓትን ተከትሎ ብዙ ቁጥር የሆነው የቱ ነው

ሀ. ተማሪዎች   ለ. አናብስቶች   ሐ. ቃላቶች   መ. መምህራኖች

34. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች መካከል በኃላፊ ጊዜ የተገለጸው የቱ ነው?

ሀ. እናቱ ከነገ ወዲያ ትመጣለች።

ለ. በደንብ ስለአነበብኩ ፈተናውን እሰራዋለሁ።

ሐ. ቁርሴን በልቻለሁ።

መ. ልብስ እያጠብኩ ነው።



LIVEWORKSHEETS

35. አቤል መትንኮ በመቸገሩ ወደ ክፍለ ሀገር ሳይሔድ ቀረ፡፡ በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተጸዖ ስም የሆነው የቱ ነው?

ሀ. መትንኮ ለ. አቤል ሐ. ክፍለ ሀገር መ. መቸገር

36. ጎበዝ ተማሪዎች ዘወትር ያነባሉ፡፡ በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ጊዜ አመልካች ተውሳከ ግስ

ሀ. ጎበዝ ለ. ተማሪ ሐ. ዘወትር መ. ያነባሉ

37. እኛ ተማሪዎች በርትተን በመስራት ሀገራችንን መለወጥ ይጠበቅብናል፡፡ በሚለው ውስጥ ተውላጠ ስም የሚሆነው

ሀ. ተማሪዎች ለ. በርትተን ሐ. መስራት መ. እኛ

38. ነጭ ቀሚስ የለበሰችዋ ልጅ የምትኖረው ከእኛ ሰፈር ነው፡፡ በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ገላጭ ሆኖ የገባው ቃል የቱ ነው?

ሀ. ልጅ ለ. ቀሚስ ሐ. ነጭ መ. ሰፈር

39. ልጆቹ ጥሩ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ የሚለው ዓረፍተ ነገር የተነገረበት ጊዜ

ሀ. ኃላፊ ለ. የአሁን ጊዜ ሐ. የወደፊት ጊዜ መ. የዘንድ አንቀጽ

40. ቀጥተኛ ያልሆነው አገላለጽ የቱ ነው?

ሀ. ሐኪሙ ህመምተኞቹን እያገላበጠ መረመራቸው፡፡

ለ. እናቱ ምሳዬን ሰጠችኝ፡፡

ሐ. መምህራችን ለተሳሳትንባቸው ጥያቄዎች እርማት ሰጡን፡፡

መ. ተዘበራርቀው የተቀመጡት ወንበሮች በአስተናጋጁ ተስተካከሉ፡፡



LIVEWORKSHEETS